በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ የሥራ ዓመት
2ኛ መደበኛ ጉባኤ ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም
የይ/መ/ቁ/804/16

ይግባኝ ባይ፡- አቶ ዘመረ ጀማነህ

ተጠሪ :- ወ/ሮ አልማዝ አስፋው

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የአጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በይግባኝ በቀረበ መዝገብ ላይ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ እና የተሰጠ የውሳኔ</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 02/04/2016 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ አትርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም፡-

1ኛ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቀድሞ በሀግ የፈረሰን ጋብቻ በድጋሚ እንዲፈርስ የፍቺ ውሳኔ መስጠቱ ከተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት፣ ባለፈ በተደመው ፍቺ ውሳኔ መሠረት በከፍፍል ያገኘሁትን ንብረት ድርሻዬን እንደገና የጋራ ንብረት ያደረገ በመሆኑ በሕገመንግሥቱ ጥበቃ የተደረገለትን የንብረት መብቱን የሚጋፋ ነው፣

2ኛ) በሀግ በሚጸና አኳኋን የተመሰረተ ጋብቻ (ቤተሰብ) የህብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ ጥበቃ ማግኘት እንዳለበት ኢትዮጵያ መነሻ በመሆኑ ከመንግስትና ከማህበረሰብ በቂ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት ተረጋግጦ እያለ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ውስጥ አለመሆናቸውን የሚያሳይ በ2009 ዓ.ም ጋብቻን ለመመዝገብ በሀግ ስልጣን ከተሰጠው ወሳኝ ኩነት መስሪያ ቤት ማስረጃ ቀርቦ እያለ ጋብቻ አለ በማለት በተግባር ለሌለ ጋብቻ ህጋዊ እውቅና ተሰጥቶ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ህገ መንግስቱ ለጋብቻ የሰጠውን ክብርና ጥበቃ የሚጥስ ነው፣

3ኛ) የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የፍቺ ውሳኔ አግባብነት ባለው የክርክር ሂደት ሳይሻር የሥር ፍርድ ቤትን ፍርድ ወደጎን በመተው የሰበር ችሎቱ የፍቺ ወሳኔ መሥጠቱ፣ የፍርድ

ቤቶችን የጸኝነት ልዕልና በሚጣረስ ነው፡ ስለሆነ በውሳኔው ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጠበት ጠይቀዋል፡፡

በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ በይግባኝ ባይ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ የተጀመረ የኃብቻ ፍቺ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ በቀን 16/04/2011 ዓ/ም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ ከይግባኝ ባይ ጋር በ23/5/1957 ዓ/ም ጋብቻ ፈጽመን ሰንኖር በመካከላችን ተፈጥሮ በነበረ አለመግባባት የተነሳ ጋብቻችን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 142607 በቀን 01/11/2001 ዓ/ም ፍች ተወስኖ የንብረት ክፍፍሉም ተወስኖ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በይግባኝ በከፍተኛ ፍ/ቤትና በጠ/ፍ/ቤት በነበረ ክርክር በእርቅ እንድንፈርስ በተሰጠን ምክር መሰረት በ24/8/2004 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት ፈርሶ የነበረ ትዳራችን እንደገና እንዲተመል ንብረት ሰመከፋፈል በሂደት የነበረው እና ሊሎች መገዛዘችም የነበረን ክርክር ተቋርጠ ንብረታችን የጋራ በማድረግ ተስማምተናል፡፡

ከዚህም በኋላ እስከ አሁን ድረስ በትዳር ሰንኖር ቆይተናል፡፡ ይሁን እንጂ አለመግባባት የተፈጠረ በመሆኑ በ29/3/1965 ዓ/ም የፈጸምነው ጋብቻ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ይግባኝ ባይ ለቀረበው አቤቱታ በሰጡት መልስ በግራ ቀኙ መካከል ጥር 5 ቀን 1965 ዓ/ም የተፈጸመው ጋብቻ ተጠሪ ባቀረቡት የፍቺ ጥያቄ ፈርሶ ንብረት ክፍፍል ተደርጎ የመጨረሻ እልባት ባገኘ ጉዳይ ላይ የፈረሰው ጋብቻ እንዳልፈረሰ ተቆጥሮ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ተጠሪ መብትና ጥቅም የሊላቸው መሆኑን፡ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት (ውሳኔ) ካገኘ በኋላ በድጋሚ የቀረበ ነስ ጠድቅ እንዲሆን የመጀመሪያ ደረጃ መታወጣያ አትርቧል፡፡

በፍሬ ነገር ላይ ደግሞ ሚያዝያ 24 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት ሁለቱኛው ፓራግራፍ ላይ መሰረት አስቀድሞ የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ በመፍረሱ እንደገና በአዲስ መልክ ሀጋዊ ጋብቻ በማድረግ በሰላም አብሮ ለመኖር ከስምምነት መደረሱን እንጅ ተጠሪ እንደሚሉት ፈርሶ የነበረው ትዳር እንዲተመል የተደረገ ስምምነት ካለመኖሩም በላይ በውለ ላይ የተመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው አዲስ ሕጋዊ ጋብቻ ለመመስረት ከስምምነት የተደረሰ ቢሆንም እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ባለመተግበራቸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕገ መንግስት ዳኞች አጣሪ ጉባዔ በስምምነቱ መሠረት የተፈጸመ ጋብቻ ካለመኖሩም በላይ ተጠሪ ያላግባ

ወይንም የፍቺ የምስክር ወረቀት ያወጡ በመሆኑና የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ አብሮ ያልኖሩ፡ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ውስጥ ያለው ቁጥሩ 405 የሆነው የጋራ ቤት እና ሌሎች የጋራ ንብረቶች ላይ ክፍፍል እድርገው በአፈፃፀም ላይ ስለሚገኝ የተረበው ክስ ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ጥቢቱም ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በይግባኝ ባይ በኩል ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል የተነሳውን መቃወሚያ ላይ ብይን ለመስጠት የግራ ቀኙ ጋብቻ በ2001 ዓ/ም በፍቺ የፈረሰው እንደገና መቀጠል አለመቀጠሉን፡ ግራ ቀኙ ከፍቺ በኋላ ጋብቻቸውን እድሰው መኖር አለመኖራቸውን፡ በ2001 ዓ/ም በፍቺ ፈርሷል የተባለው ጋብቻ ግራ ቀኙ ባደረጉት የእርቅ ስምምነት መሰረት የፍቺ ውሳኔውን ቀሪ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም የሚለው ሞግዚት አብሮ መታየት ያለበት በመሆኑ በተለይም በፍቺ የፈረሰው ጋብቻ እንደገና መቀጠል አለመቀጠሉን ለማረጋገጥ የግራ ቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ አድርጓል፡፡

ጥቢቱም ምስክሮችን ከሰማ በሁዋላ መዝገቡን መርምሮ ግራ ቀኙ ሚያዝያ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ባደረጉት ንብረት በማጣመር አብሮ ለመኖር ያደረጉት ስምምነት አዲስ ጋብቻ ፈጽመው ያላቸውን ንብረቶችን በማጣመር አብረው ለመኖር ያደረጉት ስምምነት ፍርድ ቤት መዕደቱ አዲስ ጋብቻ መመስረቱን ወይንም መታደሱን ከሚያመለክት በቀር በፍርድ ቤት የተሰጠውን የፍቺ ውሳኔን ቀሪ የማያደርግና ስምምነቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ጋብቻ እንደተደረገ ስለሚያስቆጥር ጥር 29 ቀን 1965 ዓ/ም በከብር መዝገብ ሽም ፊት በተፈፀመው ጋብቻ ላይ በድጋሚ ፍቺ ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡

የይግባኝ ባይ እና ተጠሪ የትዳር ግንኙነት ከፈረሰ በኋላ በጋብቻ ለመቀጠል ተስማምተው ፈርሶ የነበረው ትዳር የተመለሰ መሆኑንና አስተማሪ በመሆኑ በሚዲያ መነገሩ የተባደ ባለመሆኑና ግራ ቀኙ ተለያይተው የሚኖሩት በስምምነት በመሆኑ ጋብቻቸው እልቀጠለም የሚያስብል ባለመሆኑ እና ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞዎቹ ተጋቢዎች እንደገና አብሮ በመኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ከተረጋገጠ ጋብቻ ለመፈፀሙ የሕግ ግምት እንደሚወሰድ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23021 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ይግባኝ ባይ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት አዲስ ጋብቻ ባለመፈፀሙ ግንኙነቱ እልቀጠለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

የግራ ቸኮ የተደሞ ንብቻ ከፈረሰ በኋላ ንብቻውን ለማደስ መተረታቸውና በፍርድ ቤ
መጽደቁ ፡ የፈረሰው ንብቻ መመለሱ በተለያየ ሚዲያዎች መነገሩ እንዲሁም ግራ ቸ
ከእርቁ በኋላ የትዳር ግንኙነታቸው መቋጠሉ ከይግባኝ ባይ ምስክሮች ታል ይልቅ በተጠ
ምስክሮች በተሻለ በመረጋገጡ እና በግራ ቸኮ ስምምነት መሠረት አዲስ ንብ
አልተፈፀመም የሚለው የይግባኝ ባይ ክርክርም በሰበር ሰሚው ችሎት አስገዳጅ ውሳ
መሠረት የንብቻ ውኔታ መኖሩ መረጋገጥ ብቻ በቂ በመሆኑና የፈረሰው ንብቻ መቋጠሉ
ተጠሪ በተሻለ ሁኔታ ያስረዱ በመሆኑ የግራ ቸኮ ያላግባ እና የፍቺ ሰርትፍኬ
ማጠላለታቸው ወይንም ደግሞ በዕርቅ ስምምነቱ ላይ የተቋጠጠ ቅድመ ሁኔታዎች
አለመሟላታቸው በይግባኝ ባይ እና ተጠሪ መካከል ንብቻ ሆለም የሚያስብል አይደለም።

ስለሆነም ግራ ቸኮ ከላይ በተጠቀሰው አግባብ የእርቅ ስምምነት ከተደረገበት ከሚያዝያ 2
ቸን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ንብቻ ፈጽመው እየኖሩ መሆናቸውን በመረጋገጡ ተጠሪ በጠየቁ
መሠረት የነበረው ንብቻ እንዲፈረስ ወሳኔ ሰጥቷል።

ግራ ቸኮ በውሳኔው ላይ ቅር በመሰኘት በተለያየ መዝገብ ላይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍር
ቤት ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ላይ በማጣመር ከመረመረ በኋላ በግራ ቸ
መካከል የነበረው ንብቻ በፍርድ ቤት ወሳኔ እንዲፈርስ ከተደረገ በኃላ በይግባኝ በከፍተ
ፍ/ቤት እና በጠቅላይ ፍ/ቤት በነበረ ክርክር ጉዳዩን በእርቅ እንዲጨረሱ በተሰጠ ምክ
መሰረት የቤተሰብ ጉባኤ ተሰይሞ በ24/08/2004 ዓ.ም ዝርዝር የዕርቅ ስምምነ
ግራቸኮ ያደረጉ ሲሆን በዚህ የእርቅ ስምምነት ላይም ግራ ቸኮ አዲስ ንብቻ በመፈፀ
አብረው ለመኖር ከስምምነት ላይ የደረሱ መሆኑ ተመልክቷል።

በመሆኑም ከዚህ የእርቅ ስምምነት መረዳት እንደሚቻለው በግራ ቸኮ መካከል የነበረ
ንብቻ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 14607 በተሰጠ የፍቺ ወሳኔ የፈረ
ስለመሆኑ ሲሆን ከዚህ አንፃር ተጠሪ ከይግባኝ ባይ ጋር የነበረን ንብቻ በ24/08/2004 ዓ.ም
በተደረገ የእርቅ ስምምነት ፈርሶ የነበረው ትዳር እንደገና እንዲጥመል ተደርጓል ይበል
እንጂ ከእርቅ ስምምነቱ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቸኮ አዲስ ንብቻ ለመፈጸም
የተስማሙ ስለመሆኑ በመሆኑ በ1965 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሽም ፊት ያደረጉት ንብቻ
በ2001 ዓ.ም ፍርሷል ብሏል።

በግራ ቀኙ ምስክሮች ከእርት ስምምነቱ በኃላም ቢሆን ግራ ቀኙ አብረው አለመኖራቸውን ያስረዱ ሲሆን ይህም የሆነው በእርት ስምምነቱ መሰረት ባለመፈጸሙ መሆኑን የአመልካች ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ግራ ቀኙ በ24/8/2004 ዓ.ም ባደረጉት የእርት ስምምነት ላይ አዲስ ጋብቻ ለመመስረት ስምምነት ላይ የደረሱ ቢሆንም በዚህ መሰረት የተደረገ ጋብቻ ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ላይ ጋብቻ ከሚፈጸምባቸው መንገዶች ማለትም በብሄራዊ ጋብቻ፣ ሀይማኖታዊ ጋብቻ እና የባህል ጋብቻ መሆናቸው የተገለፀ ሲሆን በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የፈፀሙት ጋብቻ ስለመኖሩ ያላስረዱ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት ያለው ጋብቻ አልተፈጸመም፡፡

ከዚህ አንፃር ተጠሪ ያተረፉትን የጋብቻ ይፍረሰልኝ ጥያቄን አልተቀበለውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል በ24/8/2004 ዓ.ም የተደረገው ጋብቻ እንዲፈርስ ከተደረገ በኋላ በህግ አግባብ የተፈፀመ ጋብቻ ሳይኖር (በሁኔታ ጋብቻ መኖሩ ተረጋግጧል) በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀጽ 348(1) መሰረት በመሻር ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙ በ1957 ዓ.ም በሀገር ባህል ጋብቻ መስርተው በ1965 ዓ.ም በክብር መዝገብ ቤትም ፊት ቀርበው ጋብቻ ፈጽመው እስከ በፍርድ ቤት ፍቺ ውሳኔ የተሰጠበት 01/11/2011 ዓ.ም ድረስ በጋብቻ አብረው የቆዩ መሆናቸው እና የፍቺ ውሳኔ በመጥው ጋብቻቸውን ለመቋጠል 24/08/2004 ዓ.ም ስምምነት ማድረጋቸው በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ያልተካደ ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የፍቺ ውሳኔ ሆነ የንብረት ክፍፍል ከርክር በመጥው በጋብቻ ለመቀጠል ስምምነት አድርገው በትዳር የቆዩ መሆናቸውን በማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ እንደ አዲስ የጋብቻ ስነ-ስርአት አልተፈጸመም በማለት የሚፈርስ ጋብቻ የለም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት አሰገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያላደረገ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔውን ሽሮታል፡፡

በሌላ በኩል የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የትዳር ግንኙነት አስ ሊል የሰጠውን የውሳኔ ክፍል አጽንቶታል፡፡ ይሁን እንጂ ጋብቻው የሚፈርስ ከሆነ ከመጭ

ጀምሮ ነው የሚሰሙን በተመለከተ በከብር መዝገብ ሽም ፊት ተርበው ያደረጉት ጋብቻ 1965 ዓ.ም መወሰን ሲገባው ስምምነት ያደረጉበትን 24/08/2004 ዓ.ም መሰረት በማድረግ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል በ23/03/1965 ዓ.ም በከብር መዝገብ ሽም ፊት የፈጸሙት ጋብቻ የሰር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከ10/02/2012 ዓ.ም ጀምሮ በፍቺ እንዲፈርስ በማለት ወስኗል። ይግባኝ ባይ በውሳኔው ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል።

ይግባኝ ባይ ለሀገ መንግስት ጉዳዮች አማሪ ጉበኤ ፍርድ ቤቶች፣ የሰጡት ውሳኔ ህገ መንግስታዊ መብቴን የሚጥስ ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጥበት በማለት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ጉባኤው መዝገቡን መርምሮ በአብላጫ ድምፅ በልዩነት ትርጉም አያስፈልግውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

ይግባኝ ባይ ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍ/ቤቱ ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አንጻር ተመርምሯል። የይግባኝ ባይ ዋና ትሬታ ከተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በፍ/ቤት ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል ከርክር በምናደርግበት ጠት በፍ/ቤቱ አነሳሽነት የእርቅ ስምምነት አድርገን በአዲስ መልክ ጋብቻችን እንድንቀጥል ተስማምተናል።

ሆኖም ግን በእርቅ ስምምነቱ መሠረት የተቀመጡት ሁኔታዎች በተጠሪ በኩል ባለመፈጸማቸው ምክንያት የተፈጸመው የእርቅ ስምምነት ተግባራዊ አልተደረገም። ግራ ቀኝችንም በስምምነቱ መሠረት በጋብቻ ውስጥ አልቀጠልንም፣ ይልቁንስ ተጠሪ የፊቺ ሰርተፊኬትና ያላገባ ሰርተፊኬት ካወጡ በኋላ እንደገና ጋብቻ እንደነበረን በመቁጠር የፍች አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት ያልነበረው ሆኖ እያለ በ1969 ዓ.ም የተፈጸመው ጋብቻ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት ቀጥሏል ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ በፈጸጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጽናቱ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠልኝን መብት ይጥሳል የሚል ነው።

የግራ ቀኙ ክርክር በ24/08/2004 ዓ.ም "የተፈጸመ" በተባለው የእርቅ ስምምነት ላይ መነሻ ያደረገ ነው። ይህ የእርቅ ስምምነት በእንድ በኩል በይግባኝ ባይ እና በተጠሪ ፣ በሌላ በኩል በይግባኝ ባይ እና የይግባኝ ባይ ልጅ በሆኑት በሎቱ ዳዊት ዘመረ መካከል የተፈጸመ ስምምነት ነው።

በደግሻኝ ባይ እና በተጠሪ መካከል የተፈጸመው የእርቅ ስምምነት "የጋራ ሃብታችንን በአንድ ላይ በማጣመር አዲስ ንብረት በመፈፀም አብረን ስመኖር ተስማምተናል" የሚል ነው፡፡ በዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሱት ተዴም ሲል 1969ዓ.ም ተመስርቶ የነበረው ንብረት በ2001 ዓ.ም ላይ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ የፈረሰ ስለነበረ ነው፡፡

ግራ ቀኙ "አዲስ ንብረት እንመሰርታለን" ባሉት መሰረት ንብረት የፈጸሙ ስመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ የፌዯራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቢሆን የእርቅ ስምምነቱን ተመልክቶ ከመመዝገብ ባለፈ ፡፡ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ንብረት ተፈጽሟል፡፡ የሚል መደምደሚያ አልሰጠም፡፡

የፌዯራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችልት ፡፡በግራ ቀኙ መካከል ንብረት አለ የሚሰው ንብረት ከፈረሰ በኋላ ይግባኝ ባይ እና ተጠሪ አብረው መኖር የቀጠለ በመሆኑ በመካከላቸው ንብረት እንዳለ ይገመታል" በሚል ነው፡፡ (ገለፃ መጋቢት)

በዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ተዴም ሲል በሰ/መ/ቁጥር 23021 (ቅጽ 5) ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ በመመስረት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 23021 የተሰጠው ውሳኔ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 አፈጻጸም ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ መነሻው በአንቀጽ 95 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ ረገዴ ንብረት ስለመፈጸሙ በዋናነት የሚቀርበው የንብረት የምስክር ወረቀት ቢሆንም የንብረት የምስክር ወረቀት በሌሊ ጊዜ ንብረት የተፈጸመ መሆኑን የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ንብረት መፈጸሙን ማስረዳት የሚቻል መሆኑን ሕጉ ይደነግጋል፡፡

ንብረት መፈጸሙን ከንብረት ምስክር ወረቀት ውጪ በሆነ ማስረጃ ማረጋገጥ ወይም ማስረዳት የአጠቃላይ መርህ (ንብረትን በንብረት የምስክር ወረቀት የማስረዳት መርህ) ልዩ ሁኔታ (exemption) በመሆኑ በጠባቡ የሚተረጎም መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህ ረገዴ በተሻሻለው ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 95 የተመለከተው "የትዳር ሁኔታ መኖር" ሊረጋገጥ የሚገባው በተከራካሪዎች መካከል በሕጉ በተቀመጠው ሶስት የንብረት አፈጻጸም ውስጥ በአንዱ ተፈጸሞና ፀንቶ ያለ ሲሆን ነው፡፡

በመሆኑም "ንብረት አለኝ የሚለው ወገን ንብረቱ በሕጉ ከተመለከቱት ሶስት የንብረት አፈጻጸም ስርዓት ውስጥ በአንዱ የተፈጸመና ፀንቶ ያለ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 95 ንባብም ቢሆን ይህንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡

ከዚህ ውጪ ተከራካሪ ወገኖች እራሳቸውን እንደባልና ሚስት መቁጠራቸው ወይም ማሀበረሰቡ እንደ ባልና ሚስት የሚቆጠሳቸው መሆኑ ብቻውን ጋብቻ ለመፈጸሙ እንደ ብቸኛ ማስረጃ ሊወሰድ የሚችል አይደለም።

ከዚህም አንጻር የሰበር ችሎቱ "የጋብቻ ሁኔታ መኖር የሚለውን የተረጎመበት ሁኔታ "በጋብቻ" እና "ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር" የሚለውን የሚያደበላልት ነው። በውጤቱም በነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች መካከል ያለውን የልዩነት ጻር ድንበር የማይለይ ነው።

ውሳኔው በአስገዳጅነት የሚፈጸም በመሆኑም አዲስ ወይም ተጨማሪ የጋብቻ መፈጸሚያ ስርአትን የሚደነግግ ነው። ይህ ደግሞ በሕገ መንግስቱ ለሕግ አውጪው ተለይቶ የተሰጠን የሕግ ማውጣት ስልጣን የሚተላለፍ ነው።

ከጋብቻ ሁኔታ ጋር በተገናኘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ በአስገዳጅ የሕግ ትርጉምነት እንዲፈጸሙ አድርጓል። አንደኛው "ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ሳያፈርሱ ተለያይተው ከቆዩ ጋብቻው በሁኔታ እንደፈረሰ ይቆጠራል' የሚል ሲሆን ሌላው "ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን ካፈረሱ በኋላ ተመልሰው አብረው መኖር ከጀመሱ ጋብቻው እንደተጠሰ ይቆጠራል" የሚለው ነው።

አንደኛው ጋብቻን በሁኔታ ያፈርሳል ሌላው ጋብቻን በሁኔታ ይፈጥራል። ይህ ሁኔታ አንዱ የሌላው ግልባጭ መሆኑን ያሳያል። የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የፌዴራሽን ምክር ቤት መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም 5ኛ ፖርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት መደበኛ ጉባኤ ፡፡የሰበር ሰሚው ችሎት በሕግ አውጪው አካል የወጣውን ሕግ የመተርጎም እንጂ በሕግ ላይ የሌለን ነገር በትርጉም ሰበብ ሕግ ለማውጣት ስልጣን የለውም' በማለት የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ሽሮታል።

በተመሳሳይ ሁኔታ "አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻቸውን ካፈረሱ በኋላ አብረው መኖራቸው ጋብቻው እንደተጠሰ ይቆጠራል' የሚለው በሕግ አውጪው የማይታወቅ አዲስ የጋብቻ አፈጻጸም ስርአትን የሚደነግግ ነው። በመሆኑም በሕገ መንግስቱ ለሕግ አውጪ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ነው።

ስለሆነም በሰበር ችሎቱም ሆነ በስር ፍርድ ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 55 ስሕግ አውጪው የተሰጠውን ሕግ የማውጣት ስልጣን፣ በአንቀጽ 79(3) ላይ ‹‹ዳኞች በሕግ ብቻ ይመራሉ›› የሚለውን ድንጋጌ የሚተላለፍ ነው፡፡

ከዚህም የተነሳ የሰበር ችሎቱም ሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችል አይደለም፡፡

በ2001 ዓ.ም ላይ የፈረሰን ጋብቻ ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ እንደታደሰ በመቁጠር አዲስ የፍቺ ውሳኔ የተሰጠበት ሁኔታ ግራ ተጉ ከ2001 በኋላ በግል ያፈሩት ሃብት ወይም እዳ ቢኖር በጋራ እንዲከፈሉት የሚያደርግ ስለሆነ ውሳኔው የይግባኝ ባይን የንብረት የማፍራት መብት እና ትክክለኛ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጥስ ነው፡፡ በመሆኑም በሰበር ችሎቱም ሆነ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች ሕገ መንግስቱን የሚጥሱ ስለሆነ ሊሻሩ ይገባል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የበታች ፍ/ቤቶችም ሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሰጡት ውሳኔ ጋብቻ በሕግ ከተደነገገው የጋብቻ መፈፀሚያ ሥርዓት ውጪ በሁኔታ ጋብቻ እንደሌለ ሁሉ በሁኔታ ፍቺም እንደሌለ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምፅ መስኗል፡፡ ስለሆነም የዕርቅ ስምምነት ነጥቦች በባህል ወይም በሃይማኖት ወይም በማዘጋጃ ቤት ሹም ፊት ያልተፈፀመን የጋብቻ ጋብቻ ነው ማለት ስለማይቻል ጠ/ፍ/ቤቱ የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያሰፈፅም የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን እንዲያውቀው የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. ይግባኝ ባይ አቶ ዘመረ ጀማነህ ያቀረበት ይግባኝ በምክር ቤቱ ተቀባይነት እንዳገኘ አውቀው እንዲከታተሉ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡